ቀን፡ 30/11/2018

ቁጥር፡ GCLTR 009/18

# ጋዜጣዊ መግለጫ

አለም ዓቀፍ የጣና መልሶ ማቋቋም ማህበር ጣና ሀይቅ ላይ የተከሰተውን የእምቦጭ አረም ለማስወገድ ከተቋቋምበት ጊዜ አንስቶ የተቀናጀ ተግባር ስናከናውን መቆየታችን ይታወሳል፡፡ ከምንሰጣቸው ዘርፈ በዙ  ድጋፎች ዋና ዋናዎቹ፡- የአቅም ግንባታ ሥልጣና፣ የማሽን ልገሳና እንዲሁም የሪፖርትና ክትትል ድጋፍ ማድረግን ያካትታል፡፡

ቀደም ሲል ከለገስነው የአረም ማስወገጃ ተጨማሪ በተለያዩ የአሜሪካና የአውሮፓ ከተሞች ያሰባሰብነውን ገንዘብ በመጠቀም ሁለት H-9 905 የተሰኙ እያንዳንዳቸው 75 የፈረስ ጉልበት ያላቸው በአንድ ጊዜ  26.2 ሜትሪክ ኪዩብ አረም ማጨድ የሚችሉ ማሽኖች ከነሙሉ መለዋወጫቸው ካናዳ ከሚገኘው አኳማሪን ከተሰኘ ኩባንያ ገዝተናል። ማሽኖቹ በድምሩ 345,949 የአሜሪካን ዶላር (ወይም 10 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር) ወጭ ተደርጎባቸዋል፡፡  የማህበራችን የሳይንስ ኮሚቴ እንዳረጋገጠው ማሽኖቹ ከፍተኛ የማጨድ ጉልበት ያላቸውና በአሁኑ ወቅት የተደረገ ያለውን የአንቦጭ ማስወገድ ርብርብ በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያግዙ ተገንዝበናል፡፡ እንደኮሚቴው ገለጻ ከዚህ በፊት ከተገዛው H 5-200 ማጨጃ ማሽን ጋር ሲነጻጸር አዲሶቹ ማሽኖቸ እያንዳንዳቸው በአምስት እጥፍ አረም የማስወገድና የመሸከም አቅም እንዳላቸው በጥናት አረጋግጧል፡፡

ማሽኖቹን ለመግዛት በተደረገው የገቢ ማሰባሰቢያ መርሃ-ግብር በዲሲ፤ ዳላስ፤ ቺካጎ፣ ለንደንና አውስትራሊያ የሚገኙ የጣና ሀይቅ ወዳጆችና መላው አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ ማህበራችን በነዚህ ፕሮግራሞች በመሳተፍ የሚችሉትን ሁሉ ላበረከቱ ዜጎች ምስጋናችን ላቅ ያለ ነው፡፡ የዋሺንግተን ዲሲ የኢት/ኦ/ተ/ ደብረገነት መድሃኒያለም ቤተክርስቲያንም 70,000 /ሰባ ሽህ/ የአሜሪካ ዶላር ለማህበራችን በመለገስ ጣናን ለመታደግ የሚደረገውን ጥረት እንደምተደግፍ በተግባር ከማሳየትም ባሻገር መላው የቤተክርስቲያኒቷ ምዕምን የጣናን ጉዳይ እንደራስ በመውሰድ በገንዘብ፣በጉልበትና እንዲሁም በፀሎት ያደረጉትን ትጋት ማህበራችን በአርዓያነቱ የሚጠቀስ እንደሆነ ከምስጋና ጋር ለመግለጽ ይወዳል፡፡

የተለያዩ መርሃ-ግብሮቻችን በማስተዋወቅና እንዲሁም የእንቦጭን አረም አደገኛነት በመገንዘብ ህብረተሰቡን ግንዛቤ በማስጨበጥ ረገድ አብራችሁን ለሰራችሁ የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች በዚሁ አጋጣሚ በጎ ተግባራችሁን ለማመስገን እንወዳለን፡፡

የማሽን ግዥው ስኬታማ ሆኖ እንዲጠናቀቅ  በገንዘብ በጉልበትና በጊዜ ለጣና ሀይቅ መልሶ ማቋቋም ዘላቂ ሥራዎች ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላደረጉ አካላት በሙሉ በማህበሩ ሥም ምስጋናችን  እያቀረብ በቀጣይም ጣናን ለመታደግ በሚደረገው ጥረት በውጭ የምትኖሩ ዜጎች መልካም ተግባራችሁና ድጋፋችሁ እንደማይለየን ባለሙሉ ተስፋ ነን፡፡

GLOBAL COALITION
GCLTR
FOR LAKE TANA RESTORATION

ያለ ምንም ልዩነት ለጣና ጤንነት!!

እሸቴ ምስጋና

የአለም ዓቀፍ የጣና ሀይቅ መልሶ ማቋቋም ማህበር

የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር